ለልጆቻችሁ ትክክለኛውን ዐቂዳ አስተምሯቸው።

የእስልምና ሀይማኖት ስነ እምነታዊ (ዐቂዳ) ስነ ህግ (ፊቅህ) እና ስነ ምግባራዊ (አኽላቅ) ዐ ይት ክፍሎችን ይዟል። ከነዚህ ክፍሎቹ ውስጥ ስነ እምነታዊ አሳቦቹ ለሌሎቹ እንደ መሰረት ስለሆኑ ከሌሎቹ ክፍሎች በተለየ መልኩ ቅድሚያ ሊሰጣቸውና ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል። በደካማና በተሳሳተ ዐቂዳ ላይ የተገነባ ግብርም ሆነ ስነ ምግባር የተስተካከለ አይሆንም። በተለይ በአሁኑ ጊዜ የምናስተውላቸው የግብረ ገብነት መጥፋትና የሽሪዐህ ድንጋጌዎች መጣስ ዋነኛ መንስኤ ነገረ መለኮትን (ዐቂዳን) ከትክክለኛ ምንጩ ያለመውሰድና ያለመማር ውጤት ነው።

ስለሆነም በተለይ ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ ይህን ትክክለኛ ኢስላማዊ ዐቂደህ ተምረው ሊያድጉ የግድ ይላል።

አሳቦቹ ቀለል ይሉ ዘንዳ በጥያቄና መልስ መልኩ ተዘጋጅተዋል።

አቡ ሱሀይል

ለልጆቻችሁ ትክክለኛውን ዐቂዳህ(እምነት)አስተምሩ

ጥ: ስነ እምነታዊ አሳቦችን ከየት ነው የምንይዘው?

መ: ከቁርአንና ከሐዲስ

ጥ: አላህ ﷻ የት ነው?

መ: የት የሚለው ጥያቄ ቦታን ተፈልጎበት ከሆነ ስለ አላህ አይጠየቅበትም። ምክንያቱም አላህ ﷻ ያለቦታ ያለ ነው። በእውቀቱና በጥበቃው ደግሞ ከእኛ ጋር ነው።

ጥ: ከቁርአን ውስጥ አላህ ﷻ ያለ ቦታ ለመኖሩ ማስረጃችን ምንድን ነው?

መ: ((إن الله لغني عن العالمين)

{አላህ ﷻ ከዐለማት በእርግጥም ተብቃቂ ነው}

ጥ: ((استوى على العرش الرحمنማለት ምን ማለት ነው?

መ: ይህ ማለት ታላቁ የቁርአን ተንታኝ ኢብኑ ጀሪር አል ጦበሪይ(ረ.ዐ)እንዳሉት"አላህ ﷻ በዐርሽ ላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመሸጋገርና የመነሳት ከፍታ ሳይሆን:በመቆጣጠርና በስልጣን ከፍታ ከበላዮ ሆነ ማለት ነው።

ጥ: አላህ ﷻ እኛን(ፍጡራንን)ይመስላልን?

መ: ፈፅሞ አይመስልም

ጥ: ከቁርአን ውስጥ አላህ ﷻ እኛን እንደማይመስል ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ((ليس كمثله شيئ

{የሚመስለው ምንም ነገር የለም}

ጥ: የአላህ ﷻ ስሞች ብዛት ምን ያክል ነው?

መ: 99

ጥ: የአላህ ﷻ ስሞች 99 ለመሆናቸው ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ማስረጃችን ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት{ለአላህ ﷻ 99 ስሞች አሉት:የሰበሰባቸው ጀነትን ገባት}የሚለው የሰዪደሰችን ሀዲስ ነው።

ጥ: የአላህ ﷻ ባህሪያቶች መለኪያ ህጋችን ምንድን ነው?

መ: የአላህ ﷻን ባህሪያቶች የምንለካበት መርህ ይህ ነው{አላህ ﷻ የምሉእነት መገለጫ በሆኑ ባህሪያቶች የተገለፀና ጉድለት ከተባለ ሁላ የፀዳ ነው}።

ጥ: ተውሂድ ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ተውሂድ ማለት እውነተኛና ብቸኛ አምላክ አላህ ﷻ መሆኑን ማመን(በልብ ማስረፅ)ማለት ነው።

ጥ: ሺርክ ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ሺርክ ማለት ከአላህ ﷻ ጋር ሌላን ማምለክ ነው።

ጥ: ተውሂድ ክፍሎች አሉት?

መ: ተውሂድን መከፋፈል አዲስ የተፈጠረ ፈጠራ(ቢድዐህ)ነው፣በኢስላም ውስጥ ተውሂድን መከፋፈል የሚባል ነገር የለም።

ጥ: ላ ኢላህ ኢልለሏህ ማለት ምን ማለት ነው?

መ: በእውነት የሚገዙት ከአላህ ﷻ ውጪ የለም ማለት ነው።

ጥ: ዒባደህ ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ዒባደህ ማለት የምተገዛውን እንደ አምላክ በማሰብ ለሱ መተናነስና መዋረድ ነው።

ጥ: ከዒባዳዎች ሁላ የላቀው ዒባደህ ምንድን ነው?

መ: በአላህ ﷻ ብቸኛ አምላክነት ማመን(ተውሂድ)

ጥ: ከወንጀሎች ሁላ ከባዱ ወንጀል ምንድን ነው?

መ: በአላህ ﷻ ላይ ማጋራት(ሺርክ)

ጥ: አላህ ﷻ ጋኔኖችንና የሰው ልጆችን ለምምድን ነው የፈጠረው?

መ: ምንም ሳያጋሩበት እንዲገዙት

ጥ: ከቁርአን ውስጥ ለዚህ ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ማስረጃው((وما خلقت الجن والإنس إلا ليعبدون

{ጋኔንንም ሆነ የሰውን ልጅ እኔን ሊገዙኝ ቢሆን እንጂ አልፈጠርኳቸውም}የሚለው አንቀፅ ነው።

ጥ: ((ليعبدونማለት ምን ማለት ነው?

መ: በብቸኝነት ሊያመልኩኝ ማለት ነው።

ጥ: ከአላህ ﷻ ውጪ ያለን ማምለክ ይፈቀዳል?

መ: ፈፅሞ አይፈቀድም

ጥ: ከአላህ ﷻ ውጪ የሆነን መገዛት እንደማይፈቀድ ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ማስረጃው((وقضى ربك ألا تعبدوا إلا إياه

(ጌታህ እሱን ብቻ እንጂ እንዳታመልኩ ፈረደ)የሚለው አንቀፅ ነው።

ጥ: ሀይማኖት(ዲን)ምንድን ነው?

መ: ዲን ማለት አላህ ﷻ በነቢዩ አማካኝነት ያስቀመጣቸው መርሆች ማለት ነው።

ጥ: ኢስላም ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ኢስላም ማለት ከአላህ ﷻ እጅ መስጠትና ማጎብደድ ማለት ነው።

ጥ: የእስልምና ሀይማኖት ልክ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ማስረጃው((إن الدين عند الله الإسلام

{በእርግጥም አላህ ﷻ ዘንዳ ሀይማኖት ማለት እስልምና ነው}የሚለው ነው።

ጥ: ከእስልምና ውጭ ያለ ሀይማኖትን መከተል እንደማይፈቀድ ማስረጃው ምንድን ነው?

መ: ማስረጃው ይህ አንቀፅ ነው

ومن يبتغ غير الإسلام دينا فلن يقبل منه وهو في الآخرة من الخاسرين)

{ከእስልምና ሌላ ሀይማኖትን የሚፈለግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም።እርሱ በመጨረሻይቱም ዐለም ከከሳሪዎቹ ነው።}

ጥ: የኢስላም መሰረቶች ስንት ናቸው?

መ: አምስት ናቸው።እነሱም:—

1–ከአላህ ﷻ ውጪ በእውነት የሚመለክ የለም ሙሀመድም የአላህ ﷺ መልእክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር።

2–ሶላትን በአግባቡ መስገድ። 3–ዘካን በአግባቡ ማውጣት። 4–የረመዷንን ወር መፆም።

5–የሀጅን ተግባር መፈፀም ናቸው።

ጥ: ኢማን ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ኢማን ማለት በልብ እውነት ብሎ አምኖ መቀበል ማለት ነው።

ጥ: የኢማን መሰረቶች ስንት ናቸው?

መ: ስድስት ናቸው።እነሱም:–

1–በአላህ ﷻ ማመን 2–በመላአክቶቹ ማመን 3–በመፀሀፍቶቹ ማመን

4–በመልእክተኞቹ ማመን 5–በመጨረሻው ቀን ማመንና 6–መልካምም ሆነ መጥፎ ውሳኔዎች ከአላህ ﷻ ነው ብሎ ማመን ናቸው።

ጥ: ኢህሳን ማለት ምን ማለት ነው?

መ: ኢህሳን ማለት አላህን ﷻ እንደምታየው ሆነህ ያንን ካልቻልክ ደግሞ እሱ እንደሚያይህ ሆነህ መገዛት ማለት ነው።

ጥ: የኢህሳን መሰረቶች ስንት ናቸው?

መ: የኢህሳን መሰረት አንድ ነው፣እሱም የአላህን ﷻ አብሮነትና ተቆጣጣሪነት በማሰብ እራስን በአምልኮዎች ውስጥ ማስገኘት ነው።

==========

ለልጆቻችሁ አስተምሯቸው ለሌሎችም አስተላልፉ

አቡ ሱሀይል